# ወጣቶች በቤት ክርስቲያን



በወጣትነትህ ዘመን ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

## ወጣቶች ከቡሄ እስከ መስቀል በዓል

በሀገራችን በሚከበሩት መንፈሳውያን በዓላት ሁሉ ወጣቶች ከዓዋቂዎች የተለየ ባህልና ሥርዓት እንዳላቸው የታወቀ ነው ። በዚህም መሠረት በዓመት ውስጥ ለምናከብራቸው መንፈሳውያን በዓላት ሁሉ ልዩ ልዩ ዝግጅት አድርገው ይቆዩና ወቅቱን በመመልከት ጨዋታቸውም ሆነ ዝግጅታቸው የተለያየ ቅርጽና ይዘት ይኖረዋል ።

ከቡሄ እስከ መስቀል ባሉት በዓላት ማለት ለደብረ ታቦር ፣ ለቅዱስ ዮሐንስና ለመስቀል የሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ለልደት ፣ ለጥምቀትና ለትንሣኤ በዓላት ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ጋር አይመሳሰሉም ። ስለሆነም ወጣቶች ከቡሄ እስከ መስቀል በዓል ድረስ የሚያደርጉት ዝግጅትና የጭወታ ዓይነት እንደየሀገሩ ባህል የተለያየ ቢሆንም ጥቂቱንና በአንዳንድ ሀገሮች ሲካሄዱ ያየናቸውን ለማስታወስ እንሞክራለን ።

### የቡሄ ጅራፍ

የጅራፍ ማጮህ ጨዋታ የሚከናወነው ከቡሄ እስከመስቀል በዓል ባሉት ጊዜያት ሲሆን ይህ በዓል ከመድረሱ በፊት ወጣቶች ለጅራፍ የሚሆናቸውን ልጥ ለማግኘት ልጥ ያላቸውን እንጨቶች እየፈለጉ ይልጡና ያከማቻሉ ። በቆላማውና በወይና ደጋው ክፍል ያሉት ልጡን የሚያገኙት ከጠድቻ ከላንቁሶና ከውልክፍ ከሌሎችም እንጨቶች ሲሆን በደጋው ክፍል የሚኖሩት ደግሞ ከጓሳ ፣ ከቱቻ ሣርና ከፈረስ ጭራ ነው ፣ በዚህ ዝግጅት ከቆዩ በኋላ የቡሄ ዋዜማ ጅራፍ ይጐነጐናል ይገመዳል፣ እንዲጮህም ሆኖ ይዘጋጃል በከፍተኛ ድምጽም እንዲጮህ የሚያደርገውም በጅራፉ ጫፍ ላይ የሚገመደው ቃጫ ወይ የፈረስ ጭራ ነው ።

የቡሄ በዓል ዕለት ከዘመድ አዝማድ፣ ከአበልጅና ከጎረቤት የሚመጣላቸውን የቡሄ ኅብስት እየያዙ አመቺ በሚሆን ሜዳ ላይ የአንድ አካባቢ ልጆች አንድ ላይ እየተሰበሰቡ ዳቧቸውን እያዋጡ /እየቀላቀሉ/ “ ቡሄ በሉ ልጆች ሁሉ” እያሉ ዳቧቸውን እየበሉ ጅራፋቸውን እያጮሁ ሲደሰቱ ይውላሉ ።

በቀድሞ ጊዜ በአንዳንድ ሀገሮች በጅራፍ የመጋረፍ ባህል ስለነበር ወጣቶቹ ወገን ለይተው ቡድን አበጅተው ርስ በርሳቸው በጅራፍ ይጋረፉ እንደነበር ከአባቶች የሚነገር እውነተኛ ታሪክ አለ ። ይህም የሚሆነው በ1ኛ ደረጃ የወጣቶቹን ወኔ ለመፈተንና በጦርነትም ጊዜ ድፍረት እንዲኖራቸው ለማለማመድ ይመስላል ። በሌላ በኩል ግን ደም ካልፈሰሰ እህል ሊሆን አይችልም በሽታዎች ይበዙና ሰዎች ያልቃሉ ፣ጦርነት ይነሣና በሀገር ላይ ሰላም ይታጣል ወዘተ የሚሉትን ምክንያቶች በሚያስከትል አጉል ባሕልና ልማድ ነበር ይባላል ። ከዚህ የተነሣ ወጣቶች በጅራፍ የሚጀምሩት ግብግብ ወደ ኀልማሶቹ እየተዛመተ ጉራዴ እስከመማዘዝና ጥይት እስከመታኮስ እየደረሱ የብዙዎች አካል ከመጉደሉም በላይ በዚሁ መንሥኤ የሚሞቱ ብዙ ሰዎች እንደነበሩ ይነገራል ። ይህም በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በአዋጅ ተከልክሎ እንደቀረ አባቶች ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ ጅራፍ የማጮሁ ባህል አሁንም በአብዛኛው በባላገር ያሉ ወጣቶች ዘንድ የማይቋረጥ ነው ። ስለሆነም ጅራፍ የሚያገለግለው ከቡሄ እስከመስቀል በዓል ስለሆነ ለቡሄ ለቅዱስ ዮሐንስና ለመስቀል እያጮሁ ከተጠቀሙበት በኋላ ለእርሻ በሮች መግረፊያና ለከብት ማሠሪያ ይሆን ዘንድ ወጣቶቹ ለቤተሰቦቻቸው ይሰጧቸዋል ።

### የችቦ መብራት

የችቦ አበራር ባህልም ለቡሄ ፣ ለዘመን መለወጫና ለመስቀል በዓል የሚፈጸምና የተለመደም በመሆኑ በከተማም ሆነ በገጠር ያሉ ወጣቶች ለመብራት የሚሆን ችቦ በማዘጋጀት በኩል ታላቅ ድርሻ አላቸው ። በተለይም በባላገር ያሉ ወጣቶች ችቦውን የሚያዘጋጁት እንደከተማዎቹ ወጣቶች በቀላሉ ከባህርዛፍ ቅጠልና ጭራሮ ሳይሆን ከእንጨቶች መካከል ለዚህ ተግባር አመቺየሆኑትንእየቀጠቀጡየሚያዘጋጁ

ት ገና በበጋው ወራት ነው።የመብራቱ
ምሥጢርና ምሳሌውም ደግሞ ብሩህ
ወደሆነው አዲስ ዘመን በሰላም አሸጋግ
ረን እያሉ መጭውን ዓመት ብሩህ በሆ
ነ ተስፋ ለመቀበል ነው ። የደመራ ዕለ
ትም የብርሃነ መስቀሉንና የደመራው
ን ታሪክ በማስታወስ በየደጁ ሲበራ ለ
ዚህ ተግባር ግንባር ቀደም የሚሆኑት
ወጣቶች ናቸው ።

## የሆያ ሆዬ ጨዋታ

ከቡሄ እስከ መስቀል ባሉት ዕለታት
በባላገር ያሉ ወጣቶች ቀንና ሰዓት እየ
ቀጠሩ በበዓላት ቀን ማታ ማታ እየተሰ
በሰቡ በየመንደሩ በመሄድ የሆያሆዬ
ጨዋታ ይጨፍራሉ ። በዚህ ጨዋታ
ልምምድና ችሎታ ያላቸውና ምራቃቸ
ቸውን የዋጡ ጠንከር ያሉ ወጣቶች ተ
መርጠው ጨዋታውን እንዲመሩ ይደ
ረግና በነሱ ግንባር ቀደምትነት ተራ በ
ተራ በየመንደሩ እየዞሩ ይጨፍራሉ በ
ጨዋታው ወቅት አለመግባባት ቢፈ
ጠርየሚዳኙ ገንዘብየሚቀበሉናየሚ
ይዙ እነዚያው ናቸው ።በአንዳንድ ሀገ
ር ጨዋታው የሚጀመረው በቡሄ ዕለት
የሚፈጸመው ለመስቀል ሲሆን በአንድ
አንድ ሀገር ደግሞ ከቅዱስ ዮሐንስ እስ
ከመስቀል ነው ።

በጨዋታው ወቅት ማለት ወጣቶቹ
በየመንደሩ እየዞሩ በሚጨፍሩበት ጊዜ
በመንገድ ሳሉ ፣ ከሰው ቤት ሲገቡና ሲ
ወጡ ፣ ገንዘብ ሲቀበሉ ወይም ሲያጡ
የሚጨ ወቷቸው ጨዋታዎችና የ
ሚገጥሟቸው ግጥሞችየተለያዩ ስለሆኑ
ከመንገድ ላይ መሆናቸውን ወይም
ከሰው ቤት መግባታቸውን ማግኘ
ትና ማጣታቸውን ጭምር በሩቅ ሆ
ነው የሚያዳምጡ ሁሉ በቀላሉ ሊያውቁ
ይችላሉ ከበሩ ሲገቡ ጀምረው እስከ ሚ
ወጡበት ጊዜ ድረስ የባለቤቱን የሚስ
ቲቱንና የልጆቹን ስም እየጠሩ ያሞግ
ሳሉ አሞግሰውና ጨፍረው ሳይሰጥ ካሰ
ናበታቸው በግጥም እየተሳደቡ ይወጣ
ሉ እንዲያውም በቀድሞ ዘመን ከቤት
ከወጡ በኋላ ገንዘብ የከለከላቸውን ሰ
ውዬ ስም እያነሱ ከማልቀሳቸውም በላ
ይ ማዶ ለማዶ ሆነው በከፍተኛ ድምጽ
"እገሌ ሞቷልና አላቅሱኝ ተብላችኋ
ል" እያሉ እየተጠራሩና እያረገዱ ሙሾ
እያወጡ እያለቀሱ በቤቱ አካባቢ መቃ
ብር ቆፍረው በሰውየው ምሳሌ አንድ
ነገር ቀብረው ይሄዱእንደነበርና ያም
ቦታ የእገሌ መቃብር እየተባለ ይሰየም
እንደነበር ይነገራል ። ይህም በመሆኑ
ሰዎች ሁሉ ስማቸው እንዳይጠፋና ሰው
እንዳይስቅባቸው ወጣቶቹ በሚጨፍ
ሩበት ጊዜ በአክብሮት ተቀብለው ያቅ
ማቸውን ሰጥተው ይሸኛሉ እንጂ አይ
ከለክሉም ነበር ። አሁንም ሰው የመሰ
ደቡና በቁም የመቀበሩ ጉዳይ ይቅር
እንጂ የሆያሆዬ ጭፍራ በአንዳንድ ሀ
ገሮች እስካሁን ድረስ ያልቀረ መሆኑ
የተረጋገጠ ነው ።

ከመስቀል በዓል በኋላ ጭፋሮው ሲ
ያከትምና መንደሮቹ ሲዳረሱ ያለው ገ
ንዘብ ተቆጥሮ እንደ ገንዘቡ ብዛትና ማ
ነስ እንደጨፋሪውም ሰው ብዛት ተተ
ምኖ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰንጋ ይ
ገዛና በጭፋሮው የደከሙት ወጣቶች
ብቻ ተሰብስበው በጫካ ውስጥ
ወይም በባዶ ቤት አርደው ያንን ራሳ
ቸው ተራ በተራ እየቀቀሉ እስካለቀ ድ
ረስ እየዘፈኑ እንዲበሉ ይደረጋል ።በመ
ጨረሻም ሥጋውን ሲጨርሱ ቆዳው ለ
ጠፍር ይሆናቸው ዘንድ ሰንጥቀው ያን
ን በእጣ ተከፋፍለው ይለያዩና ጠፍሩ
ን አልፍተው ለቤተሰቦቻቸው ያበረክ
ታሉ ራሳቸውን ችለው በትዳር ላይ ያሉ
ትም ለምራን ፣ ለማነቆና ለመርገጥ ለ
ጅራፍና ለመጫኛ እያደረጉ እራሳቸው
ይጠቀሙበታል ።

## ሴቶች ወጣቶች በዕንቁጣጣሽ

በየዓመቱ የዕንቁጣጣሽ እለት ልጃገ
ረዶች ሁሉ በአንድነት ተሰብስበው
"እንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽ በ
አበባ አሽብርቅሽ" እያሉ በመዝፈን በ
ዓሉን በደስታ ያሳልፉታል ።ይልቁንም
በአንድ ላይ ከተሰበሰቡ በኋላ" አበባዬ
ሆይ ለምለም" እያሉና ሌላም ዘፈን እ
የዘፈኑ በሠፈራቸው ውስጥ ባሉት መን
ደሮች እየገቡ ገንዘብ ይሰበስባሉ ልጃገ
ረዶቹ በመንደር ውስጥ በሚገቡበት
ጊዜ በከተማ ውስጥ ያሉ እናቶች ገንዘ
ብ ሲሰጡ በገጠር ያሉት ግን እህል ፈት
ልና ጥጥ የመሳሰሉትንም ጭምር ይሰ
ጧቸዋል እነሱም ይህንን ተቀብለው
ከመከፋፈላቸው በፊት ካገኙት ነገር
ሁሉ ከፍለው በሠፈር ውስጥ ጧሪ ለሌ
ላቸው ባልቴቶች የሚሰጡ አሉ ።

ይህ ሁሉ ከባህላችን ጥቂቱ ክፍል
ስለሆነ መጥፎው ታርሞ የሚሻሻለው
ተሻሽሎ ለአሁኑ ትውልድና ለአለንበ
ት ዘመን ተስማሚ የሆነው ተበጥሮና
ተንጠርጥሮ በሥነ ሥርዓት እንዲካ
ሄድ ቢደረግ ለወጣቶቹ መዝናኛ ከመ
ሆኑም በላይ የአባቶችንም ባህልና ታሪ
ክ ለማስታወስ ሊጠቅም ይችላል ።የጅ
ራፍ ማጮሁና የሆያሆዬው ጭፈራ በከ
ተማ ውስጥ አስቸጋሪ ይመስላል ምክን
ያቱ ቀደም ባለው ጊዜ እንዳየነው በየ
መንገዱ የሚጮህው ጅራፍ ጆሮ እያደ
ነቆረ አላፊ አግዳሚውን ያስቸግር እን
ደነበር የሚታወስ ነውና እንዲቀር መደ
ረጉ አግባብ ነው ። የሆያ ሆዬ
ጭፈራውም እንዲሁ የሚያስከትለው
ችግር አለ ። ይኸውም በከተማ ውስጥ
ብዙዎች ርስበርሳቸው ለመተዋወቅ ስ
ለማይችሉ ከየጉዳናው እየተጠራቀሙ
ስለሚጨፍሩ ከነሱ ጋር ማን አብሮ እን
ዳለ ባለመታወቁ ለሌባ አመቺ መንገድ
ከመፍጠሩም በላይ ጨፋሪዎችም ቢሆ
ኑ በገንዘብ ክፍያው እየተጣሉ መደባደ
ባቸው አልቀረም በዚህ ግርግር ጉልበት
ያላቸው ብቻ ገንዘቡን እየተናጠቁት
ስለሚሄዱ አቅመ ደካማው ወጣት ትር
ፉ ጩኸት ብቻ ነው ስለዚህ ባሕሉም
ሆነ ሥርዓቱ እንደገጠሩ ስላልሆነ ከአባ
ቶች ባህል ውጭ ነውና ቢታሰብበት
መልካም ነው ።

ትንሣኤ : መጽሔት
ቁጥር 48
መስከረም 1974.